# እ.ኤ.አ ከጁን 1-10/2019 የነበረው


# የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎቸ ላይ ከዕለት ወደ ዕለት ተጠናክሮ ነበር የተሰተዋሉት፡፡ በተለይም በምዕራብ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና ደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በይበልጥ ከመጠናከራቸዉም ባሻገር አልፎ አልፎ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደነበረ የተመዘገቡ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በአንዳንድ የሰሜን ሱማሌ፣ አፋር እና ምስራቅ ትግራይ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በደብረማርቆስ 44.7 እና 48.4፣ በነጆ 65.1፣ በአርጆ 38.8፣ በነቀምቴ 41.8 እና 54.5፣ በሀረማያ 42.0፣ በሳዉላ 30.8፣ በአርባ ምንጭ 40.3፣ በቡሌሆራ 63.6፣ በምዕራብ አባያ 68.8፣ በጅማ 44.0፣ 35.0 እና 34.5፣ በጎሬ 40.0፣ በሻሁራ 38.8፣ በአይራ 40.3፣ በቡሬ 32.0፣ በሀረር 63.0፣ በጅግጅጋ 34.8፣ በአቦቦ 32.1 እና 31.4፣ በእምድብር 38.0 እና 33.1፣ በወላይታ ሶዶ 53.7 እና 54.9፣ በቦሬ 49.0፣ በቡለን 34.1፣ በጋምቤላ 40.0፣ በበደሌ 33.0፣ በአዶላ 140.8(እጅግ ከባድ ዝናብ)፣ በደሎመና 68.0፣ በደገሃቡር 34.2፣ በያቤሎ 118.8(ከባድ ዝናብ) እና በቴፒ 48.2 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በምዕራብ ትግራይ፣ በሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ በምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ከምስራቅ ሸዋ፣ ምዕራብ ሀረርጌ እና ከአንዳንድ የአርሲ ዞኖች በስተቀር በሁሉም የኦሮሚያ ክልል ዞኖች ላይ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብ ህዝቦች እና ጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ ከዋርዴር፣ ከጎዴ እና ጥቂት የሲቲ ዞኖች በስተቀር በሁሉም የሱማሌ ክልል ዞኖች ላይ እና በአፋር ክልል ዞን 01 ላይ ከ25-200 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ለ2-10 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ፣ በአፋር ክልል ዞን 3፣ 4፣ 5 እና 2፣ በምስራቅ ሸዋ፣ አርሲ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ከሱማሌ ክልል በጎዴ እና በአፍዴር ዞኖች ላይም ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2 ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ ዝናብ ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር ከጥቂት የኢሉአባቦራ፣ የምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ፣ ከአፍዴር፣ አርሲ እና ከጎዴ ዞኖች በስተቀር በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ ስርጭት ነበራቸዉ፡፡(ካርታ 3) ።


ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 3   ኢ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




## እ.ኤ.አ ከጁን 1-10/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ

## በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

ባሳለፍነው የመጀመሪያዎቹ የጁን አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ ሚቲዎሮሎጂካል ክስተቶች በምዕራብ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና ደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከነበራቸዉ የዝናብ ጥንካሬ ጋር ተያይዞ የተሻለ ዕርጥበት አግኝተዋል፡፡በመሆኑም በአብዛኛው መኸር አብቃይ አካባቢዎች የተገኘዉ ዕርጥበት አስቀድመው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የተለያዩ ሰብሎች እና ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በመካሄድ ላይ ለሚገኘዉ የወቅቱ የግብርና ሥራ ዕንቅስቃሴ ማለትም ለማሣ ዝግጅት፣ለዘር፣ በተጨማሪም ለመኸር ዝናብ ተጠቃሚ ለሆኑት የአርብቶና ከፊል አርብቶአደር አካባቢዎች የተገኘው ዕርጥበት ለግጦሽ ሳር ፣ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት እና ለመሳሳሉት የግብርና ተግባራት አመቺና የጎላ ጠቀሜታ እንደነበረዉ መገንዘብ ተችሏል፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2019 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# <u>እ.ኤ.አ ከጁን 01-10/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>

# <u>በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደርው ተፅዕኖ</u>

እ.ኤ.አ 01-10 ጁን 2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ ሰሜናዊ እና ደቡባዊ አባይ፣ የላይኛው ኦሞጊቤ፣ መካከለኛው ስምጥሸለቆ፣ ጥቂት የላይኛው ባሮአኮቦ፣ <u>ምእራባዊ</u> አጋማሽ ገናሌዳዋ እና መካከለኛው ዋቢሸበሌ ኪስ ቦታዎች እንዲሁም ጥቂት የላይኛው ባሮአኮቦ ተፋሰሶች ከፍተኛ የሆነ እርጥበት አግኝተዋል። በተጨማሪም እርጥበታማና መጠነኛ እርጥበት የተሰተዋለባቸው ተፋሰሶች በጥቂት የታችኛው ተከዜ ፣ምስራቃዊ እና መካከለኛዉ አባይ፣ ምስራቃዊ ባሮ አኮቦ፣ መካከለኛውና የታችኛዉ ኦሞጊቤ፣ የላይኛዉ ስምጥሸለቆ ፣መካከለኛዉ ገናሌዳዋ፣ መካከለኛዉ ዋቢሸበሌ፣ የላይኛዉ እና የታችኛዉ አዋሽ፣ የላይኛዉ ኡጋዴን፣ ጥቂት ምስራቃዊ አፋር ደናክል ተፋሰሶች ናቸው። በተቀሩት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በከፊል ደረቅና ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተሰተውሏል። በተለይ አፋር ደናክል፣ ኦጋዴን፣ የታችኛው ዋቢሸበሌና የተከዜ ምስራቃዊ አጋማሽ ተፋሰሶች ላይ የነበረው ደረቅ ሁኔታ ከቀኑ ሙቀት ጋር ተዳምሮ በውሃ ሀብት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው (ካርታ 5) ።

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2019 ድረስ በተፋሰሶች ላይየነበረው የእርጥበት መጠን



# <u>እ.ኤ.አ ከጁን 11-20/2019 የሚኖረው</u>

## <u>የአየር ሁኔታ አዝማሚያ</u>

በጁን ሁለተኛው አሥር ቀናት በመደበኛ ሁኔታ በደቡብ ምዕራብ፣በምዕራብ፣በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛው አካባቢዎች ላይ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ የሚሄዱ ሲሆን፤ በአንጻሩ በሰሜንና በሰሜን ምሥራቅ ላይ አልፎ አልፎ ከሚኖረው መጠነኛ ዝናብ በስተቀር ደረቅና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ያመዝናል።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደ ቀን እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ ስለሚጠበቅ፤በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት <u>ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ኢሉአባቦራ፣የሰሜንና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣የሰሜንና የደቡብ የጎንደር ዞኖች፣የባህር ዳር ዙሪያ፣ሰሜን ሸዋ ፤ የትግራይ መካከለኛውና ምዕራባዊ ዞኖች፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ክልሎች ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሀዲያና የጉራጌ፣ የወላይታ፣ የዳውሮ ፣የጋሞጎፋ፣የከፋና የቤንች ማጂ እንዲሁም ሲዳማ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ሊከሰት ይችላል።በሌላ በኩል የአርሲና የባሌ ዞኖች ፣ከአፋር ዞን 3 እና 5 ፣ ሐረሪ፣ ድሬዳዋ፣ጅግጅጋና ሲቲ ዞኖች ከሚኖራቸው የተጠናከረ የደመና ሥርጭት በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ። የተቀሩት የሀገሪቱ ዞኖች ግን ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።</u>

## እ.ኤ.አ. ከጁን 11-20/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ

ከላይ በተሰጠው ትንበያ መሠረት በጁን ሁለተኛው አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደ ቀን እየተጠናከሩ እንደሚሄዱና በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት ሊኖር እንደሚችል ይህም ሁኔታ በመኸር ወቅት ለሚከናወነው የግብርና እንቅስቃሴ ጥሩ አስተዋፅኦ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በትንበያው ላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚጠበቀው ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል አንፃር አስቀድመው የተዘሩና በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግም ሆነ በመዘራትና በቡቃያ ደረጃ ለሚገኙ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለተለያዩ የቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሀ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ከዝናቡ መብዛት ጋር ተከትሎ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከፍተኛ እርጥበት በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በሚገኙ አካባቢዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት፣ እንዲሁም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ከአፈር መሸርሸርም ሆነ ከመሬት መንሸራተት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ሊያስከትል ስለሚችል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነዉ፡፡ በተጨማሪም የሚጠበቀው ዝናብ የደረሱ የበልግ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ በየጣልቃው የሚኖሩትን ደረቅ ቀናት በመጠቀም የሰብል ስብሰባ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ በሌላም በኩል በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው መጠነኛ እርጥበት በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት ካገኙት እርጥበት ጋር ተዳምሮ የመጠጥ ውሀ አቅርቦትንም ሆነ የግጦሽ ሳር ልምላሜና የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ ምንጮችን ከማጎልበት አንጻር የጎላ አስተዋጽኦ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡

# እ. ኤ. አ ከጁን 11-20/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

# አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ  ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት ውስጥ የክረምቱ እርጥበታማ ሁኔታ በብዙዎቹ ተፋሰሶች ላይ እየተሰፋፋ በመሄድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑት ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት እንደሚሰተዋል ትንበያው ያመለክታል።

ይህንን ሁኔታ ተከትሎ በአብዛኛው ኦሞጊቤ፣ባሮአኮቦ፣ ተከዜ፣ አባይ፣ስምጥሸለቆ፣ የላይኛው አዋሽ እና  የላይኛው ገናሌዳዋ  ተፋሰሶች የተሻለ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል።በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የተተነበየ በመሆኑ ይህ ሁኔታ ወራጅ ውሃ እንዲኖር አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ ለውሃ ሃብት ግብአት ይኖረዋል። በተጨማሪ በአብዛኛው አዋሽ፣የላይኛው ገናሌዳዋ፣ የላይኛዉ ዋቢ ሸበሌ፣የላይኛዉ      ኡጋዴንና አዋሳኝ ተፋሰሶች መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት ተፋሰሶች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል።